# አበሳ ነው!

አበሳ ነው አንቺን መውደድ - በፍቅርሽ ቅናት መቃጠል፣
እያወቁ እሳት ጎርሶ - ተንጨርጭሮ አሮ. . . መክሰል፤
መከራ ነው ካንቺ መወገን - በችጋር ቸነፈር መስለል፣
በቁም ሞተው እየሄዱ - ከንቱ ኗሪ መምሰል::

አንዳንዱማ «የታደለ»፣
ለወረት . . .ነዋይ ያደረ፣
ውበት አካልሽን ቸርችሮ፣
ክብር ዝናሽን ገብሮ፣
ንቀት ጥላቻውንም ረጭቶብሽ፣
ይኖራል ተደላድሎ. . .
        ሞቆ - ደምቆ በእቅፍሽ::

ጊዜ ከድቶ ያሳጣቸው - ኃይል-አልቦ የመከኑ፣
ያደርጉትን መላ ያጡ - አቅም ሽሽቶ የበገኑ፣
ከተጣባሽ ክፉ ጭራቅ - ሊያስጥሉሽም ያልቻሉ፣
«ሆነሽ» ሊያዩሽ ያለሙትን - «ሆነሽ» ሊያዩሽ ያልታደሉ፣
የሐዘን ማርሽ እንጉርጉሮ - እህህ..ን እንደዘመሩ፣
እንደ ጨው ዘር ተበታትነው - ባለም ዙሪያ ባክነው ቀሩ::

በተፈጥሮሽ ውበት የዋለለ፣
ውስጠ-ምስጢርሽን ልወቅ ያለ፣
ተጎዳ እንጂ ያስተዋለ፤
ደንቁሮማ የኖረ፣
ምንኛ የታደለ፤
ባዶ ቀፎውን ቁጭ እንዳለ፣
ሳይነካ ተገላገለ::

አንቺን . . . አንቺን ማለቱ፣
የኑሮ ቀመር ስሌቱ፣
እስር፣ እንግልት. . . ሰንሰለቱ፣
የዕድሜ ጣሪያ ሳይደርስ መሸበቱ፣
አበሳኮ ነው ውጤቱ::
ለታሪክሽ፣ ለውበትሽ . . በኃያል ፍቅር መክነፉ፣
መሸማቀቅ፣ ስደት፣ ውርደት. . አንጀት ማቁሰል ሆነ ትርፉ::
ይገርማልኮ ያለም ጣጣ፣
የሚያፈቅሩት ላያዋጣ!

ቃጠሎ ነው! ካንቺ መወለድ፣
መከራ ነው! በፍቅርሽ መንደድ፣
ስቃይ ነው! ለክብርሽ መስገድ፣
አበሳ ነው! ባንቺ መጠመድ...::

ጌታቸው አበራ
ታህሣሥ ፪ ሺ ፪ ዓ/ም
(ዲሴምበር 2009)